# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT — جبهة تحرير أورومـــو

Gaafa: 23-10-2012 تاريخ    Lakk.: No.: 017/stm-abo/2012 رقم

*ለሙስሊሙ ማህበረሰብ የመብት ጥያቄ የጥይት ምላሽ መስጠትን ተከትሎ ለሚባባሰው ቀውስ ብቸኛ ተጠያቂው የወያኔ መንግስት ራሱ ነው*
*(የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ)*

የወያኔ መንግስት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ለሃይማኖቱ ነጻነት መከበር ለበርካታ ወራት ሳያቋርጥ በሰላማዊ መንገድ እያቀረበ ላለው የመብት ጥያቄ የሃይል ምላሽ መስጠቱን እንደቀጠለ ነው። ይህን የመብት ጥያቄ በሃይል ለማፈን አስቦ እስካሁን በተለያዩ አካባቢዎች የበርካቶችን ህይወት ቀጥፏል፣ አያሌዎችን አቁስሏል፣ አስሯል።

ሰሞኑን በሰሜን ኦሮምያ ወሎ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች የወሰደውና እየወሰደ ያለው ዘግናኝ የግድያ እርምጃም ለዘመናት የዘለቁት የስርኣቱ ፋሺስታዊና ኣምባገነናዊ እርምጃዎች ቀጣይ ኣካል መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ መንግስት "የማንኛውም ሃይማኖት ነጻነት የተከበረ ነው" ብሎ ለይስሙላ በህገ መንግስቱ ላይ የጻፈውን ህግ በመጻረር መሪዎቻችንን ራሳችን እንምረጥ ብሎ ድምጹን ያሰማውን ሙስሊሙን ማህበረሰብ ሌላ ታርጋ ለጥፎበት መምታቱ በጣም ኣሳዛኝ ነው።

ይህ ጨካኝ ስርኣት የኦሮሞ ወጣቶችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ላለፉት 21 ኣመታት ሲያቀርቡ የቆዩትን የፖለቲካ መብት ጥያቄዎችን በጠመንጃ ሃይል ሲያፍንና የንጹሃንን ደም ሲያፈስ እንደኖረው ሁሉ ለሃይማኖት ነጻነት መከበር ለቀረበለት የመብት ጥያቄም እነሆ ተመሳሳይ ምላሽ እየሰጠ ይገኛል።

እነዚህ እርምጃዎች ሁሉ የሚያረጋግጡት የወያኔ መንግስት ህዝቦችንም ሆነ የሃይማኖት ማህበረሰቦችን የማይወክል ሃይል መሆኑን ነው። ስርኣቱ በጠመንጃ የሚያመልክ ሃይል እንጂ ኣስተዳድራቸዋለሁ ለሚላቸው ህዝቦች መብትና ደህንነት ምንም ኣይነት ሃላፊነት የማይሰማው መሆኑን ስልጣን ከያዘበት እለት ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ በፋሺስታዊ እርምጃዎቹ እያስመሰከረ ይገኛል።

በህዝቦች ንቀት ተሞልቶ ካበጠው ከዚህ ጥጋበኛ ስርኣት ህዝቦች ምንም የሚጠብቁት ነገር ኣይኖርም። የተያያዙትን ፍትሃዊ የመብት ጥያቄ ኣፋፍመው ስርኣቱን በሁሉም ኣቅጣጫ ወጥሮ መፈናፈኛ ከማሳጣት በቀር የቀረበላቸው ሌላ ኣማራጭ በጭራሽ ኣይታይም።

የወያኔ መንግስት ኣሁን በተያያዘው ኣካሄድ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ለበርካታ ወራት ሳያቋርጥ በሰላማዊ መንገድ ሲያቀርብ የቆየውን የሃይማኖት ነጻነት ጥያቄ ለመቀልበስ ብሎ የንጹሃንን ደም በማፍሰሱ ይጠየቅበታል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ይህ ሰፊ ማህበረሰብ በሰላማዊ መንገድ ብቻ የጀመረውና እስካሁን የሄደው ኣካሄድ ትእግስቱ ተሟጦ በሃይል ራስን ወደ መከላከል ኣማራጭ ቢያመራና በዚያም ሳቢያ ሊከሰት ለሚችለው መጠነ ሰፊ ኣደጋ በብቸኝነት የሚጠየቀው ራሱ የወያኔ መንግስት መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ሰሞኑን በገርባ ከተማና በኣካባቢው እንዲሁም ኣከታትሎ በሌሎችም ኣካባቢዎች የወያኔ መንግስት የንጹሃን ዜጎችን ደም ማፍሰሱን በጽኑ ያወግዛል። ከዚህ ኣይነቱ ኣረመኔያዊ እርምጃም እንዲገታም በኣጽንኦት ያሳስባል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር

ጥቅምት 23, 2012